# የስያትል ት/ቤቶች ጽ/ቤት በፈቃደኝነት ለሚያገለግሉ የማጣሪያ ፎርም (1ኛ ገጽ ከ4)

*ፎርሙ በአመልካች ተሞልቶ ከቀረበ በኋላ በጽ/ቤቱ አስተዳዳሪ ወይም በፕሮግራሙ ሃላፊ ተጣርቶ ይጸድቃል*

SEATTLE PUBLIC SCHOOLS

**በፈቃደኝነት የሚሰራበት ቦታ፡** ______________________

## በፈቃደኝነት የሚያገለግለው ሰው መረጃ

ስም(የመጠሪያ/ የአያት): ______________________ **የትውልድ ቀን** (ቀን/ወር/ዓመት) __________

ከጋብቻ በፊት የነበረ ስም : ______________________ ጾታ: __________

አድራሻ: ______________________ ከተማ፡ስተይት፡ዚፐ : __________

ስልክ ቁጥር: __________ ኢመይል: __________

ከስያትል ት/ቤቶች ግንኙነት ☐ወላጅ/አሳዳጊ ☐ቤተሰብ ☐የኮሚዩኒቲ አባል ☐ሌላ: __________

ተማሪ ልጅ ካለዎት የልጅዎን ስም ከዚ ቀጥለው ይጻፉ: __________

በፈቃደኝነት ሲያገለግሉ የሚያስፈልግዎት ልዩ እንክብካቤ አለ ወይ ? ☐አያስፈልገኝም ☐አዎን፡የሚያስፈግዎት አገልግሎት ያብራሩ፡

## በፈቃደኝነት ለሚያስፈልገው ሰው በአደጋ ጊዜ መጠራት ያለበት ሰው

| | | | |
|---|---|---|---|
| በአደጋ ጊዜ የሚጠራው ሰው ስም: | | ዝምድና: | |
| በአደጋ ጊዜ የሚጠራው ሰው ስልክ ቁ.: | | ኢመይል አድራሻ: | |
| የሐኪምዎ ስም: | | የሐኪምዎ ስልክ ቁ. | |

## በፈቃደኝነት ስለሚያገለግለው ሰው የግል ወይም የሥራ ምስክርነት

*ምስክርነቱ እንዳስፈላጊነቱ ማጣራት በሚደረግበት ወቅት ይሆናል። ቢያንስ አንድ በግል ሊመሰክር የሚችል እንዲሰጡ።*

| | | |
|---|---|---|
| ምስክርነት ሰጪው ሰው የመጠሪያና የአያት ስም: | ስልክ ቁጥር | ከእርስዎ ጋር ያለው/ያላት ዝምድና |
| ምስክርነት ሰጪው ሰው የመጠሪያና የአያት ስም: | ስልክ ቁጥር | ከእርስዎ ጋር ያለው/ያላት ዝምድና |

## ማገልገል የፈልጉበት ቦታና የሚገኙበት ቀንና ሰዓት

| የሚመቹኝ ቀናት: | ☐ ሰኞ | ☐ ማክሰኞ | ☐ ረቡዕ | ☐ ሐሙስ | ☐ ዓርብ | ☐ ሌላ ቀን: |
|---|---|---|---|---|---|---|
| የሚመቸኝ ሰዓት: | | | | | | |

## ለማገልገል የሚፈልጉበት በምንድነው(የአገልግሎት ዓይነት)

| | |
|---|---|
| ☐ | *ተማሪዎችን ማገዝ* → ☐1 ለ 1 ☐በትንሽ ስብስብ ☐ከክፍል ውስጥ መርዳት ☐በሌላ መንገድ: __________<br>☐ሒሳብ ☐ንባብ ☐ጽህፈት ☐ድራማ ☐ስነ-ጥበብ ☐ሙዚቃ ☐ሌላ፡ አብራራ |
| ☐ | *ማስተዳደር/ጸሃፊነት ማለት የአካዳሚ ትምህርት ያልሆነ*<br>☐በሜዳ/በምሳ ጊዜ ጥበቃ ☐ጽ/ቤት/ ቤተመጻህፍት ☐ክፍል ውስጥ ማገዝ ☐ሌላ፡ አብራራ |
| ☐ | *ስፖርት(በፈቃደኝነት ለማገልገል ከመፈቀዱ በፊት ተጨማሪ ማጣሪያ ያስፈልጋል)*<br>☐ለመካከለኛ 2ኛ ደራጃ ተማሪዎች የስፖርት አሰልጣኝ ☐በሌላ ስፖርት ቡድን ማሰልጠን: |
| ☐ | ከት/ቤ ውጭ ጉዞ ሲኖርጥበቃ* የሚቀጥለውን ያብራሩ → ☐የቀን ጉዞ ☐ሄዶ የሚታደርበት የተማሪዎች ጉዞ*<br>ቀን/ሰዓት: ቦታ: የት/ቤት ሰራተኛ ስም: |
| ☐ | *ሌላ* (ክፍል ውስጥ፣ ፕሮጀክት ሲኖር፣ ዲፓርትመንት ወይም ማሳየት የሚፈልጉት ልዩ ችሎታ ካለዎት)እባክዎን ያብራሩ: |

<< የሚከተሉት ሁለት ገጾችን እንዲሞሉ >>

# የስያትል ት/ቤቶች ጽ/ቤት በፈቃደኝነት ለሚያገለግሉ የማጣሪያ ፎርም (2ኛ ገጽ ከ4)

*ፎርሙ በኣመልካች ተሞልቶ ከቀረበ በኋላ በጽ/ቤቱ አስተዳዳሪ ወይም በፕሮግራሙ ሃላፊ ተጣርቶ ይጸድቃል*

**በፈቃደኝነት የሚሰራበት ቦታ፡** ______________________________

**<u>ደህንነትና በሃላፊነት ስለ መጠየቅ</u>**

______ ከተማሪ ጋር የሚፈጠረው መቀራረብ በጨመረ ቁጥር ተማሪው/ዋ የበለጠ እምነት በማሳደር የሚሰማውን እስከ ማካፈልድረስ ሊደርስ ይችላል። እንዲህ ዓይነት ሁኔታ ሲያጋጥም በጥሞና ማዳመጥና ርህራሄ ማሳየት። የሆነ ነገር አደርጋለሁ የሚል ቃል ከመግባት መቆጠብና የሚያሳስብ ነገር ሲኖር ለሚመለከታቸው ሪፖርት ማቅረብ ያስፈልጋል።

______ በፈቃደኝነት የሚያገለግለው ሰው ከስራው ጋር የሚዛመድ ካልሆነ በስተቀር የራሱን/የራስዋን የግል ታሪክ ከምንገር መቆጠብ ያስፈልጋል። የራስህን/ሽን እንደ ስልካ፡ አድራሻ ኢመይልና እንዲሁም የሶሺያል መገናኛ አድራሻ ለተማሪው ከመስጠት መቆጠብ።

______ እንዳንድ ተማሪዎች በተለይ የ1ኛ ደረጃ ያሉት ተሎ ብለው የመቅረብ ባህርይ አላቸው።እንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ ሲያጋጥም ጥንቃቄ መደረግ አለበት።. ለምሳሌ ፊት-ለፊት ማቀፍ(ሃግ መስጠት) አይፈቀድም ።እንዲህ ዓይነት ሁኔታ ሲያጋጥም እጅዎን በልጁ/በልጅዋ ትከሻ ላይ በማስቀመጥ በጎን ብቻ ማቀፍ ወይም ደግሞ የእጅ ሰላምታ ማለት (ሃይ ፋይፍ) መስጠት። የፈለገው ዕድሜ ላይ ይሁኑ ማንም ልጅ ጭን ላይ ማስቀመጥ **<u>በምንም</u>** ዓይነት አይፈቀድም።

**<u>የተለያየ አስተዳደግ ካላቸው ልጆች ጋር መስራት</u>**

______ በስያትል ትምህርት ቤቶች የሚማሩ ተማሪዎ ከተለያየ ባህል፣ልምድና ህብረተሰብ ካላቸው ቤተሰብ የመጡ ናቸው። ስለሆነም ከተማሪዎች ጋር በሚሰሩበት ወቅት የእያንዳንዱን ተማሪ ባህልና ልምድ ከግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል። ስለዚህ የልጆቹን ባህል ወይም ልምድ መረዳትና ልጁም የትምህርት ቤቱን ልምድ/አሰራር እንዲረዳ ማገዝ የልጆቹን የመማር ችሎታ ያጎለብተዋል።ሌላ መታወስ ያለበት ደግሞ የራስህን/ሽን ባህል፣ ልምድ ወይም እምነት በልጆቹ ላይ ለማሳደር መሞከር አይፈቀድም።

**<u>መረጃን በምስጢር ስለመያዝ</u>**

______ በስያትል ትምህርት ቤቶች የሚማሩ ተማሪዎችን የሚረዱ ሰዎች የተማሪዎችን ኢንፎርሜሽን በሚስጥር እንደሚይዙ መተማመን ይችላሉ። በተጨማሪም የእያንዳንዱ ተማሪ በትምህርት ቤት ውስጥ የሚገኝ ማነኛውም ሪከርድ ወይም ኢንፈርመሽን በሚስጥር መያዝ እንዳለበት በፌደራል ህግና በቤተሰብ የትምህርት መብት( Family Educational Rights and Privacy Act (“FERPA”), 20 U.S.C. Section 1232g) ያዛል። ስለሆነም በፈቃደኝነት ተማሪዎችን የሚረዳ ማንም ሰው የተማሪዎቹን መረጃ(ኢንፍርመሽን) በሚስጥር የመያዝ ግዴታ አለበት/አለባት ማለት ነው።

______ በፈቃደኝነት ሚያግዙትን ተማሪ የሚመለከት ማንኛውም ኢንፍርመሽን በሚሰጠው መመሪያ መሰረት ከሚመለከታቸው የትምህርት ቤት ሃላፊዎች በስተቀር ለሌላ ሰው አሳልፈው እንዳይሰጡ(እንዳይናገሩ) ይጠበቅብዎታል(ሃላፊነት አለዎት)።

______ የሚረዱትን ልጅ የሚመለከት የሚያገኙት ማነኛውም መረጃ(ኢንፎርመሽን)ለልጁ/ትዋ አስተማሪ ወይም ለትምህርት ቤቱ ርእሰ-መምህር ካልሆነ በስተቀር ለሌላ ሰው ለምሳሌ፡ ለጓደኛ፣ ለባል ወይም ሚስት፣ ወይም ሌሎች የልጁን ሁኔታ ለማወቅ የሚፈልጉ ሰዎች፡ ወይም ለማህበራዊ አገልግሎት ሰራተኞች ወይም ለልጁ አያቶች ወይም የሃይማኖት ሃላፊዎች፣ ወይም ለሃኪሞች ወይም ነርሶች ማስተላለፍ/መንገር በምንም አይፈቀድም።

______ የሚረዱትን ልጅ የሚመለከት መረጃ ለሚመለከተው የት/ቤት ሰራተኛ ወይም የት/ቤት አስተዳዳሪ ጋር መነጋገር ይቻላል። በተለይ ደግሞ ስለልጁ/ልጅትዋ ጤንነት በተለይ ህክምና በአስቸኳይ የሚያስፈልጋቸው ከሆነ ወይም ልጁ በራሱ/በርስዋ ወይም በሌሎች ላይ አደጋ ለማድረስ እንደሚፈልግ ከተናገረ ወይም ከቃጣ/ከቃጣች ለሚመለከታቸው የት/ቤቱ ሰራተኞች መናገር ያስፈልጋል።

______ስለሚረዱት ልጅ ከሌሎች ሰዎች ጋር መናገር ትክክል ካለመሆኑም በላይ ሕገ-ወጥ መሆኑን ማስታወስ ያስፈልጋል።

**በፈቃደኝነት የሚያገለግል ሰው የስምምነት ቃል፡**

*እኔ(ስም ይጻፉ), ______________________________,ከላይ የተጠቀሱትን መመሪያዎችን (እንዲሁም በፈቃደኝነት ለሚያገለግሉት ሰዎች የሚመሩበት ያለውን ጽሑፍ) በፈቃደኝነት በማገለግልበት ወቅት ወይም ከእዛ በኋላ መመሪያውን እንደምከተል። ይህንን መመሪያ የያዘውን ስነ-ጽሑፍ የት ማግኘት እንደምችልና ለሚኖሩኝ ጥያቄዎችና ማሳሰቢያዎች ማንን ማነጋገር እንዳለብኝ አስፈላጊ ማብራሪያ ተሰጥቶኛል። በተጨማሪም በስያትል ት/ቤቶች በፈቃደኝነት ተማሪዎችን መርዳት ከመጀመሬ በፊት በቪድዮ የሚሰጠው ፍትወተ-ሥጋን (ሰክሸዋል) የሚመለከት( Online Adult Sexual Misconduct Video)ማየት እንዳለብኝና እንደዚሁም ካሁን በፊት የፈጸምኩት ጥፋት መኖር-አለመኖሩን እንዲጣራ ተስማምቻለሁኝ። በተጨማሪም በስያትል ትምህርት ቤቶች ውስጥ በፈቃደኝነት በማገለግልበት ውቅት የእኔ ስዕል(ፎቶ) በት/ቤቶች ጽ/ቤት መጽሔቶች ሊለጠፍ እንደሚችል ተነግሮኛል። በተጨማሪም ት/ቤት ውስጥ ከተማሪዎች ጋር መስራት ትልቅ ሃላፊነት መሆኑንና በፈቃደኝነት በማገለግልበት ወቅት የት/ቤቱ ርእሰ-መምህር/መምህርት ወይም የፕሮግራሙ ሃላፊ በማነኛውም ጊዜ የምሰጠውን አገልግሎት እንዳቋርጥ ሊነግሩኝ መብታቸው መሆኑን አውቃለሁ።*

,

| | | |
|---|---|---|
| በፈቃደኝነት የሚያገለግለው ሰው (ስም ጻፍ/ፊ) | በፈቃደኝነት የሚያገለግለው ሰው ፊርማ | ቀን |

SEATTLE PUBLIC SCHOOLS

# የስያትል ት/ቤቶች ጽ/ቤት በፈቃደኝነት ለሚያገለግሉ የማጣሪያ ፎርም (3ኛ ገጽ ከ4)

*ፎርሙ በኣመልካች ተሞልቶ ከቀረበ በኋላ በጽ/ቤቱ አስተዳዳሪ ወይም በፕሮግራሙ ሃላፊ ተጣርቶ ይጸድቃል*

**በፈቃደኝነት የሚሰራበት ቦታ :** ______________________________

**የወንጀለኛነት ታሪክ መጠየቂያ**

***ልጆችን ወይም ህጻናትን ማጎሳቆል በሚመለከት በስተይት መመሪያ ዓንቀጽ መሰረት*** (RCW 43.43.830 through 43.43.845)

የዋሺንግተን ስተይት ምክር ቤት የህጻናት ወይም ባጠቃላይ ልጆችን ደህንነት ለመጠበቅ በትምህርት ቤት ከልጆች ጋር በነጻ ለማገልገል ፈቃደኛ የሚሆኑ ሰዎች በስተይቱ ሕግ (43.43 RCW) መሰረት የወንጀለኛነት ታሪካቸው መታወቅ ስላለበት አስቀድመው ይህንን የመግለጫ ፎርም ማሟላት እንዳለባቸው ያዛል።የስያትል ትምህርት ቤቶችም የተማሪዎችን ደህነንት የመጠበቅ ሃላፊነት ስላለበት በፈቃደኝነት የሚያገለግሉ ሰዎች ማገልገል ከመጀመራቸው በፊት በየዓመቱ ይህ የሚጠየቀው የየወንጀለኛነት ማጣሪያ መደረጉን ይደግፋል።

**በፈቃደኝነት ለማገልገል የሚፈልጉ ሰዎች የወንጀለኛነት መግለጫ ጥያቄዎች አዎን ወይም አይደለም በማለት መልስ እንዲሰጡ ይጠየቃሉ**

ለጥያቄው የሚሰጡት መልስ አዎን(YES) የሚል ከሆነ ከጥያቄው ቀጥሎ ባለው ባዶ ቦታ ላይ የተከሰሱበት ወይም ያጠፉት ጥፋት ምን እንደሆነና የት ቦታ፣ መቼና ዬት ፍርድ ቤት እንደቀረቡ ማብባሪያ እንዲጽፉ ይጠየቃሉ። ለሚሰጡት ማብራሪያ የተሰጠው ባዶ ቦታ የማይበቃ ከሆነ መጨረሻ ላይ ባለው ባዶ ቦታ ያም ካልበቃ ሌላ ተጨማሪ ወረቀት በማከል ተጨማሪ ማብራሪያ መስጠት ይችላሉ።

**ሌላ መታወቅ ያለበት ደግሞ በፈቃደኝነት የሚያገለግሉ የስፖርት አሰልጣኞች፡ ወይም ተማሪዎች ውጭ የሚያድሩበት ዙረት ሲያጋጥም ልጆችን አጅበው የሚሄዱና ሌሎች ፈቃደኞች ተጨማሪ የ (FBI) ኤፍቢአይ ወይም በትምህርት ቤቶች ጽ/ቤት የሚደረግ ሌላ ተጨማሪ ማጣሪያ ሊደረግ ይችላል።*

.

| | | |
|---|---|---|
| 1) | **ወንጀል ሰርተው ተከሰው ወይም ታስረው ያውቃሉ?** | ☐የለም ☐አዎን ***መግለጫ ሰጥ*** |
| | | |
| 2) | **ከዕድሜ በታች የሆነ/የሆነች ልጅ ላይ ጉዳትወይም ዓመጽ በማድረስ ወይም ፍትወተ-ሥጋ በመፈጸም ወይም በመሞከር (ሰክሽዋል አቢዩዝ)ምክንያት በዓንቀጽ** r 13.34 RCW **መሰረት ወደ ሕግ ቀርበው ያውቃሉ ወይ?** | ☐የለም ☐አዎን ***መግለጫ ሰጥ*** |
| | | |
| 3) | **ከዕድሜ በታች ካላቸው ልጆች ጋር የጾታ ግንኙነት በመፈጸም ወይም በመሞከር ተከሰው በሕግ ዓንቀጽ** Title 26 RCW **መሰረት ፍርድ ቤት ቀርበው ያውቃሉ ወይ?** | ☐የለም ☐አዎን ***መግለጫ ሰጥ*** |
| | | |
| 4) | **ከዕድሜ በታች ከሁኑ ልጆች ጋር የጾታ ግንኙነት(ሰክሽዋል አቢዩስ) በማካሄድ ወይም ልጅ በመምታት ምክንያት እንዲህ ዓይነቱን በደል የሚመለከት ቦርድ ፊት ቀርበው በእርስዎ ላይ ውሳኔ ተሰጥቶ ያውቃል ወይ?** | ☐የለም ☐አዎን ***መግለጫ ሰጥ*** |
| | | |
| 5) | **እላይ ከተጠቀሱት ሁኔታዎች ሌላ ከወጣቶች ወይም ከህጻናት ወይም ደግሞ አካለ ስንኩላን ከሆኑ ሰዎች ጋር በታማኝነት እንዲያገለግሉ የተሰጠዎትን ሃላፊነት በሚመለከት የርስዎን የህይወት ታሪክ ጥያቄ ውስጥ ሊያስገባ የሚችል ወይም ጥርጣሬ ውስጥ ሊያስገባ የሚችል ካሁን በፊት ያገጠመዎት ነገር አለ ወይ?** | ☐የለም ☐አዎን ***መግለጫ ሰጥ*** |
| | | |

*በማመልከቻው የተጻፈውን ጽሑፍበሙሉ አንብቤዋለሁ። ማመልከቻውን በሚመለከት ስለራሴ የሰጠሁት የህይወት ታሪክ በዋሺግተን ስተይት ሕግ አንቀጽ RCW 9A.72.085 መሰረት ያልተጭበረበረና ሐቀኛ መረጃ መስጠቴን ማረጋገጥ እወዳለሁ። የስያትል ትምህርት ቤቶች ጽ/ቤትም በፈቃደኝነት እንዳገለግል ማሟላት ያለብኝ እንዳሟላሁ ለማረጋገጥ በበኩሉ እኔን የሚመልከት ማንኛውም ነገር (ኢንፎርመሽን) ማጣራት እንደሚችል። በተጨማሪም ከስያትል ት/ቤቶች ጽ/ቤት ስለ እኔ መረጃ እንዲሰጥ የሚጠየቅ ማነኛውም ሰው መረጃውን እንዲሰጥ መፍቀዴን አረጋግጣለሁ።ይሁን እንጂ ከሌሎች ስለ ራሴ የሚሰጠው መረጃ ለራሴ መሰጠት እንደሌለበትም ለማወቅ ችያለሁ። ስለዚህ ስለኔ ለስያትል ትምህርት ቤቶች ጽ/ቤት የሚሰጠው መረጃ ወይም የህይወት ታሪክ/መረጃ ለሰጪውም ሆነ ለተቀባዩ ማለት ለስያትል ት/ቤቶች ጽሕፈት ቤት ምንም ተቃውሞ እንደሌለኝ አረጋግጣለሁ።በሚያገኘው መረጃ መሰረትም የስያትል ት/ቤቶች ጽ/ቤት በፈቃደኝነት እንዳላገለግል ሊከለክለኝ እንደሚችል አውቃለሁ።*

***የቀረቡትን ጥያቄዎች በሙሉ በትክክለኛና በሐቀኝነት መልስ ካልሰጠሁ በስያትል ትምህርት ቤቶች ውስጥ በፈቃደኝነትም ይሁን ተቀጥሮ ለመስራት ሊያግደኝ እንደሚችል ይገባኛል።***

______________________________ ______________________________

**በፈቃደኝነት የሚያገለግለው ሰው (ስም ጻፍ/ፊ)** **በፈቃደኝነት የሚያገለግለው ሰው ፊርማ** **ቀን**

Please submit this completed form to your site volunteer coordinator. Thank you for your service!

*Updated: 7/2016*

SEATTLE PUBLIC SCHOOLS

# <u>የስያትል ት/ቤቶች ጽ/ቤት በፈቃደኝነት ለሚያገለግሉ የማጣሪያ ፎርም Form (4ኛ ገጽ ከ4)</u>

*ፎርሙ በኣመልካች ተሞልቶ ከቀረበ በኋላ በጽ/ቤቱ አስተዳዳሪ ወይም በፕሮግራሙ ሃላፊ ተጣርቶ ይጸድቃል*

**በፈቃደኝነት የሚሰራበት ቦታ:**

**:** ______________________________

**የአመልካቹ ስም:** (ተጨማሪ ማብራሪያ ወይም መግለጫ ካለከዚህ በታች ይጻፉ )

## >>>>>>>> VOLUNTEER SITE OFFICIAL USE ONLY <<<<<<<<

| Volunteer Clearance Item | Date | Initials | Specify/Notes |
|---|---|---|---|
| ☐ Volunteer Form 1-4 Completed | | | |
| ☐ ID Verification (Driver's Lic. or other ID with Name & DOB) | | | |
| ☐ Volunteer Handbook or Handbook Link Provided | | | |
| ☐ ASM Video Completed | | | |
| ☐ WATCH or Other Background Check clearance specify type: | | | |

______________________________ Volunteer Approver Name/Title (Print)

______________________________ Volunteer Site Approver Signature

__________ Date

Please submit this completed form to your site volunteer coordinator. Thank you for your service!